የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 34
ADDIS ABABA 20th May, 2013

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፮/፪ሺ፭ ዓ.ም

ለጎዴ-ቀብሪደሃር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከሳውዲ የልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ....................................................ገጽ ፮ሺ፰፻፶፭

CONTENTS

Proclamation No. 786/2013

Saudi Fund for Development Loan Agreement for Financing the Rural Electrification Project in Gode–Kebridehar Project Ratification Proclamation ...................................... Page 6855

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፮/፪ሺ፭

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጎዴ-ቀብሪደሃር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፶፮ሚሊዮን ፪፻፶ ሺ. የሳውዲ ሪያል (ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሣ ሺ. የሳውዲ ሪያል) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ፌብሩዋሪ ፳፰ ቀን ፪ሺ.፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፪ሺ.፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No. 786/2013

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE SAUDI FUND FOR DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Saudi Fund for Development stipulating that the Saudi Fund for Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 56,250,000 Saudi Riyals (fifty six million two hundred fifty thousand Saudi Riyals) for financing the Rural Electrification Project in Gode–Kebridehar was signed in Addis Ababa, on the 28th day of February, 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of May, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

የአንዱ ዋጋ 2:30
Unit Price

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለጐዴ-ቀብሪደሃር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከሳውዲ የልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፮/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሳውዲ የልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ፌብሩዋሪ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 5/582 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶፮ሚሊዮን ፪፻፶ሺ የሳውዲ ሪያል (ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሣ ሺ የሳውዲ ሪያል) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Saudi Fund for Development Loan Agreement for Financing the Rural Electrification Project in Gode – Kebridehar Ratification Proclamation No. 786/2013".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement Number 5/582 signed in Addis Ababa, on the 28th day of February, 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Saudi Fund for Development is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 56,250,000 Saudi Riyals (fifty six million two hundred fifty thousand Saudi Riyals) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 20th day of May, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት